# <u>ሰውን ከእንስሳ የሚለየው</u>

እግዚአብሄር ሰውን ሲፈጥር በአምሳሉ
ተፈጥሮን እንዲለውጥ በማሰብ ኃይሉ
ሳይንስን ጥበብን ተቀዳጅቶ እንዲኖር በትግሉ
በጾም በጸሎት አይደለም ተማጽኖ እንዲኖር በዕድሉ።

የማሰብ ኃይሉን ከጡንቻው ጋር በማጣመር
የተፈጥሮን ህግ በመረዳት በሰፊው በመመራመር
ከጨለማ ወጥቶ ብርሃንን እያየ እንዲኖር
ሰጥቶታል የማሰብ ኃይል በመጥፎ ዕድሉ እንዳያማርር።

የሰውን ልጅ ከእንስሳ የሚለየው
የማሰብ ኃይል ስላለው ነው
የቴክኖሎጂ ፣ የሳይንስ ባለቤት በመሆን ኑሮውን ውበት ለመስጠት ነው።

የሶክራትስ ፣ የፕላቶን ፍልስፍና እንደሚያስተምረን
የተፈጥሮን ህግ በመረዳት በዕውቀት በመካን
የራስን ምንነት በመረዳት ዕውነትን በመፈለግ እኩልነትን ፍትህን በማስፈን
የታሪክ ባለቤት ለመሆን ነው ለማስመስከር ብቃትነትን።

አራቱ የፕላቶን መመሪያዎች
ጥበባዊነት ሚዛናዊነት ታጋሽነትና ጉብዝና
የረዥም ጊዜ የምርምር ውጤቶች
ናቸው የሳይንስ መመራመሪያ መነሻዎች።

በእነዚህ አራት መመሪያዎች በመመስረት
አስተሳሰብን ጥራት በመስጠት
ከጨለማና ከችግር ለመላቀቅ የተፈጥሮን ህግ በመረዳት
የሳይንሱ መሰረተ ሃሳብ ነው የፍልስፍናው ዕምብርት ።

ሰውን ከእንስሳ የሚለየው
ኑሮውን ለማሻሻል የሚችል ስለሆነ ነው
የተፈጥሮን ህግጋት በመረዳት ተፈጥሮን ለመቆጣጠር የሚያስችለው
ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ የኑሮ ደረጃ ለመሸጋገር የማሰብ ኃይል ስላለው ነው።

የጥንቱ የግሪክ ፍልስፍናዎች የሂሳብና የሳይንስ ምርምሮች
የኋላ ኋላ ወደ ተግባራዊነት ሲለወጡ ያየናቸው ውጤቶች
የህንፃ የቲአትር የግጥምና የስፖርት ቅንጅቶች
የሰው ልጅ የማሰብ ኃይል ናቸው ብልጽግናዎች።

የሮማውያን ስልጣኔ ኋላም የሬናሳንስ ውብ ስራዎች
የተመሰረቱት በሶክራቶስ በፕላቶን መሰረተ ሃሳቦች
የአመጽ ሳይሆኑ የሎጂክና የማሰብ ኃይል ቅንብሮች።

አመጽና ጦርነት የደካማ አስተሳሰብ ስልቶች
ሲሉን ሲያስተምሩን የግሪክ ተመራማሪ ፈላስፋዎች
ሎጂክና ዲያሌክቲክስ ብቻ ናቸው ይሉናል የስልጣኔ ብርሃን አፈንጣቂዎች።

ሃሳቡ በዚህ የተመሰጠ ህዝብ ስራው ሁሉ ይሆናል ብሩህ
ከተንኮል ከተረባ የጸዳ አስተሳሰቡ የሚሆን ጉልህ
ቆንጆ ነገርን በመመኘት ያከናውናል ስልጣኔን በእልህ
ታሪክን ለመስራት ተልዕኮው ይሆናል ከእንግዲህ ወዲህ።

ሰውን ከእንስሳ የሚለየው
ህይወቱን በስርዓት መምራት የሚችል ፍጡር በመሆኑ ነው።

በዘመነ ሬናሳንስ የሰው ልጅ አስተሳሰብ ሲለወጥ
በጥንቱ የጨለማ ሁኔታ የሰው ልጅ መኖር ሲያቋርጥ
የተገለጠላቸው ጥቂት አዋቂዎች ሲታገሉ ለለውጥ
የቀደዱት የሳይንስ ፈለግ ሆነ የተፈጥሮ መቆጣጠሪያ የማይበለጥ።

ኬፕለር ጋውስ ላይብኒዝ የተባሉት ታላላቅ ተመራማሪዎች
በአስመሰከሩት አስደናቂ የምርምር ውጤቶች
የሰው ልጅ ተፈጥሮን እንዲያጠና በሰሩት መሳሪያዎች
ተፈጥሮን እንዲለውጥ ፣ ኑሮውን እንዲያሻሽል እንዲጥል አደረጉት የታሪክ ትዝታዎች።

በዚህ በአዲሱ የሳይንስ ምርምር መሰረት
ዐለም ያልተዘበራረቀች መሆኗ ሲደረስበት
ፕላኔቶችም መስመራቸውን ጠብቀው የሚጓዙ መሆኑ ሲከሰት
የሰው ልጅም ዕድገቱን በስርዓት እንዲያቅድ መሰረት ተጣለለት።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ስልጣኔ ዕድገት ሲባል
ሃሳበ ድውይ ያልሆነ የክስተት ቁንጽል
የብዙ ነገሮች ጥምር ሆነ የስራ ፈትል።

ስዕል ፣ ድራማና የአርክቴክችር ስራዎች
ፊዚክስ ፣ የኢኮኖሚክስና የተፈጥሮ ሳይንስ እትብትቦች
አንድ ላይ ተጣምረው የሚታዩ የተያያዙ ቅንብሮች
ሆነው መታየት ቻሉ በአንድነት ዕውነትም የስልጣኔ መሰረቶች።

ታላቁ ላይብኒዝ ባስመሰከረው ተግባራዊ ማረጋገጫ
ኢኮኖሚክስ ካለፊዚክስ የማይሆን መወጣጫ
ዕውነትም ታየ ፊዚክስ የኃይል ማመንጫ
የሰው ልጅ አንድን ነገር መለወጥ የሚችለው ሆነ በፊዚክስ ቡጥጫ።

ሰው ሰው መሆኑን የሚያረጋግጠው
እራሱንና አካባቢውን መለወጥ ሲችል ብቻ ነው።

ይህ ከሆነ የስልጣኔው ፈለግ
ለምንድነው የሚነዳው የጥቁር ህዝብ በደፈናው እንደበግ
በነጭ ኦሊጋርኪ መደብ የሚታሸው ፣ የሚጣለው እንደፈግ።

ያልተማረ ያልተመራመረ ስልጣን የያዘ
ጭንቅላቱ በሰብአዊው ጥንታዊ የግሪክ ትምህርት ያልተበረዘ
ስነ-ምግባርን ከሞራል ጋር አቀላቅሎ ራሱን ያልጠመዘዘ
እንደሚሆን የታወቀ ነው ጭንቅላቱ የቦዘዘ።

ዛሬ የምናየው በአፍሪቃ ምድር
እንደዚህ ዐይነቱን ዝባዝንኬ ክምር
የነጭ ኦሊጋርኪ መደብ አፈ ቀላጤ ውጥርጥር
ነው ፣ የጥቁርን ህዝብ ታሪክ አጉዳፊ የሆነ መሪር።

ከዚህ የውጥንቅጥ አገዛዝ ለመውጣት ያለው አማራጭ
የጥቁር ህዝብ በአዲስ የስልጣኔ ብርሃን ሲፈነጭ ነው ሲወራጭ።

የጥቁር ህዝብ ሰው መሆኑን የሚያረጋግጠው
የተጫነበትን የድንቁርና ጫና አሽቀንጥሮ ሲጥል ብቻ ነው።

የነጭ ኦሊጋርኪ መደብ የሚተበትበውን ተንኮል የተገነዘበ
ወዳጅ መስሎ መሳሪያ እያቀበለ የሚያጫርሰንን ያብጠለጠለ
የመሪዎችን ድውይ ተልዕኮ በዲያሌክቲክስ መነጽር ያገናዘበ
መነሳት ያለበት ዛሬ ነው ስልጣኔ ወይም ሞት ብሎ እየመዘገበ።

ኢትዮጵያዊ ሰው መሆኑን የሚያስመሰክረው
የጎሳን የእርስ በርስ ጥላቻን የቂም በቀልን ባህል አሽቀንጥሮ ሲጥል ብቻ ነው።

ኢትዮጵያዊ ሰው መሆኑን የሚያስመሰክረው
የስራን ትርጉም በመረዳት ስርዓት ያለው ኑሮ ሲገነባ ብቻ ነው።

ሰውን ከእንስሳ የሚለየው
በማያቋርጥ የማሰብ ኃይሉ
ከእራሱ ጥቅም ይልቅ በአንድነት ለአንድነት ታሪካዊ ድርጊትን ሲያከናውን ብቻ ነው።

እግዚአብሄር ሰውን በአምሳሉ ሲፈጥረው
ተፈጥሮን አሳምሮ ሲለግሰው
አየር እንዲተነፍስ ውሃ እንዲጠጣ ሲያድለው
በተንኮል በቂም በቀል መንፈስ ተወጥሮ
ወንድም ወንድሙን እንዲያሰቃይ አይደለም ያስተማረው።

እግዚአብሄር በአምሳሉ ሰውን ሲፈጥረው
ተፈጥሮን አስመስሎ ቆንጆ ከተማዎችን እንዲገነባ ምልክት ሲሰጠው
እርስ በርሱ እንዲገናኝ የባቡር ሀዲድ እንዲሰራ መንገዱን ሲያሳየው
የዕውቀት የቴክኖሎጂ ባለቤት ሲያደርገው
ከእንስሳ በላይ በብዙ እጅ አርቆ የማሰብ ኃይል እንዳለውም ለማስገንዘብ ነው።

**ፈቃዱ በቀለ**